# ሚሌኒየሙን ባልጫ
## ሰሞኑን በፓልቶክ ቁጥር ስምንት

**ከበልጅግ አሊ**

ሰሞኑን ወደ ፓልቶክ ክፍል ወጣ ብዬ የስድብ ማለኪዬን ባስቀመጥኩበት በደደቦች ሸንጎና በወያኔ ሲቪሊቲ ሩም ውስጥ ስመለከተው በሁለቱ ክፍል አንድ አይነት ሁኔታዎችን እንዳሉ ለመገንዘብ ችያለሁ። ሁለቱም የሚሰድቡት ኢትዮጵያዊነትን አጥብቀው ይይዛሉ የሚባሉትን ድርጅቶች ወይም ግለሰቦች ነው። እንደተለመደው ኢሕአፓ ፣ ዶክተር ታዬ ፣ አሲንባ ፓልቶክ፣ አያልነሽ፣ ኢትዬ ላየን(Ethiolion.com) ድህረ ገፅ በደደቦቹ ሸንጎ ሲብጠለጠሉ ነው የሰነበቱት።

በአሁን ግዜ ግን በተለይም በድህረ ገፆችና በየፓልቶኮች በተቀነባበረ ሁኔታ ፀረ ኢሕአፓ እንቅስቃሴዎች ተጧጡፈው ይገኛሉ ። ሁኔታው ከድሮ የተለየ የሚደርገው ቢኖር የፀረ ኢሕአፓ ቅስቀሳው በደርግና በወያኔ ቀድሞ አባሎች በተቀነባበረ ሁኔታ መቅረቡና ድርጅታዊ ይዘት ማግኘቱ ነው መሆኑ ነው። በአንዳርጋቸው ፅጌና በብርሃኑ መዋ በህዋስ የተመለመሉት ቀድሞ በምስራቅ አውሮፓ ይገኑ የነበሩት የኢሰፓ ካድሬዎች ለዚህ ቀይ ሽብራዊ አይነት ቅስቀሳ በጣም ከፍተኛ አስተዋፅኦ እያደረጉ ነው። እነዚህ የደርግ ዕርዝራዦች  የተካኑት በስድብ ላይ ስለሆነ **ቀይ ሽብር አሁኑኑ** በኢሕአፓ አባላትና ደጋፊዎች ላይ ማለት መጀመራቸው ምንም ሊያስደንቅም አይችልም።

እኔ በበኩሌ በየፓልቶኩ የቅንጅት መንፈስ እያሉ የሚያረግዱለት ምን እንደሆነ ላውቅ አልቻልኩም።በተለይ አንዳንዶቹ  የቅንጅት መንፈስ ወረደብን በማለት በቅንጀት ልሳን ነው የምንናገረው በማለት ለኢትዮጵያ ሕዝብ በማይገባው ቋንቋ እርስ በእርሳቸው ቢግባቡ የራሳቸውን ፍላጎት እንጂ ሕዝብ የደገፈውን አቋም ስለማይሆን መግባባቱ በታሪክ አንድ ወቅት አብረው በመስራታቸው ብቻ ነው ሊሆን የሚችለው። እኔ ከዚህ በመነሳት የስድብ ናዳ ማውረድ የቅንጅት መንፈስ መሆኑን ነው ልረዳ የቻልኩት። የቅንጅት አመራር የሆኑት በሌላ ስም እየገቡ መስማታቸው የአደባባይ ሚስጥር ነው። ማለትም እነ ብርሃኑም ሆነ እነ አንዳርጋቸው ይህንን ስድብ ስያቀነባብሩ እንደሚውሉ ለማንም ግልፅ ነው።  የቅንጅት መንፈስ ማለት መሳደብ መሆኑን ባያምኑበት ኖሮ አባሎቻቸውን በዚህ አፀያፊ ተግባር እንዳይካኑ ያደርጉ ነበር። ሁኔታው ግን ከዚህ የተለየ ነው። ቦዘኔዎቹን ሰብስበው፣ ቀን ሙሉ ስራ የሌላቸውን በድርጅት አሰባስበው፣  የስድባ አይነት አንዳስተማሯቸው ምንም ጥርጥር የለኝም። ስለዚህም የቅንጅት መንፈስ ምን እንደሆነ ለኔ ነው ግራ የገባኝ። ስድብ ወይስ ለነፃነት ትግል፣ ሁሉንም ያጠቃለለ ግንባር ወይስ ክፍፍል። እኔ ልጠይቀው የምፈልው በውች ያሉት የቅንጅት መሪዎች ለአባላቶቻቸው የሰጡት መመሪያ ምንድነው?

የቅንጅት መሪዎች ከኢሰፓና ደርግ ድርጊት እራሳቸውን በግልፅ ሊያገሉ ይጋባል የሚል አመለካከት አለኝ። አሁን በተለይ ከእስር ቤት በኃላ የሚጠበቅባቸው ይህ ውሉ የጠፋውን የቅንጅት ትግል ጉዞ ሊያስተካክሉት ያስፈልጋል። የቅንጅት መንፈስ ማለት ከደርግ የተወረሰ የቀይ ሽብርን ፍላጎት የተላበሰውን መጥፎ አዝማሚያ አለመሆኑን በግልፅ ለአባላቶቻቸው መመሪያ መስጠት ቀዳሚ ተግባራቸው መሆንም አለበት።

ቅንጀት ወያኔ እንደሚያናፍስው የደርግ ተቀጥላ አለመሆኑን ግልፅ አውጥተው እስከ አላስታወቁ ድረስ ወያኔ በምህራብ አለም እየዞረ ይህንኑ ዜና ማነፈሱ አይቀርም። ለዚህም በተጨባጭ ማስረጃ ወያኔ ወደ እነአንዳርጋቸው ፅጌ የደደቦች ሸንጎ የፓልቶክ ክፍል ብቅ እያለ አባላቱ የተናገሩትን እየቀዳቀ በአይጋ ፎረም ላይ ማውጣቱን ሁላችንም የምናየው ነው። ቱባ ቱባ የደርግ ካድሬዎች የነበሩትን  እዛ ክፍል ውስጥ እየተሰበሰቡ የሚደርጉትን ማንም የሚውቀው ነው። እነ ብዙ ወንድምአገኝ የደርግ ኢሰፓ ጋዜጠኛና፣ የቀይ ሽብር ቀንደኛን የሆነችውን የማያውቅ ይኖራል ብዬ አላምንም። ሌሎችም ስማቸውን ወደፊት የሚጠቀሱ ግለሰቦች ለአጠፉት የሰው ህይወት ቅንጅት መደበቂያ ወይም ተመልሶ ስልጣን ለመውጫ መሰላል መሆን የለበትም።

ሌላውም ክፍል ደግሞ የፀረ ወያኔ ክፍሉ ይዳከማል በሚል ብቻ እነዚህን አረመኔዎች ዝም ብሎ ማለፍ አያዋጣውም። ከወያኔ በኃላ ልንመሰርተው የምንፈልገው ስርአት ዴሞክራሲያዊ እንዲሆን ከተፈለገ እነዚህ የፋሽሽት ቡችላዎች ከወዲሁ ሊገቱ ይገባል አሊያ ወደ ስልጣን ቢቀርቡ የሚመጡት ቀይ ሽብር ወይም የዘር ማጥፊትን ብቻ ነው። በተለየ በቀይ ሽብር የተሰውትን ታሪክ ብቻ ሳይሆን የብዙ ሰዎች ህይወት ያጠፉትን ግለሰቦች ታሪክ ተጽፎ ሊቀመጥ ይገባል።ይህ ደግሞ ከነፎቶቸው ቢሆን ሌላ አገር ሄደው እንደ ጅቡ ቁርበት አቅርቡልኝ እንዳይሉም ያግዳል።

በኤርትራ የተፈጠረውን ግንባር ሁኔታና ስላጠፉት ገንዘብ ሲሰሩ ስለከረሙት እንቅስቃሴ እንጠየቃለን ብለው ያሰቡት እነ አንዳርጋቸውና ጀሌዎቻቸው ይህንን በመፍራት ቅራኔውን ወደ ኢሕአፓና ቅንጅት ለማድረግ ጥረት ላይ ናቸው። ወያኔን ከትግል መድረኩ በማውጣት የወያኔን ቡረካ ሲቀበሉ ከደርግ ኢሰፓ እርዝራዦችና በቀይ ሽብር ወንጀለኛነታቸው እንዳይነሳባቸው ከሚፈልጉ ደግሞ የአንጋችነት ማዕረጋቸው ይፀናላቸዋል። ከኢትዮጵያ ህዝብ የተዘረፈውንና ይዘው የፈረጠጡትን ገንዘብ እነ ካሳ ከበደ ይረጩላቸዋል። ይንን በመጠቀም የፀረ ወያኔውን ካንፕ ከመቼውም በላይ ሲያምሱት ይታያሉ ።

ትግሉ ወያኔን አውርዶ ደርግን መመለስ ሊሆን እንደማይችል እነ በዙ ወንድምአገኘሁ አልተረዱትም።ነፍስ ያጠፉ የደርግ ኢሰፓ አባለትን ከትግሉ አለማገድ ትግሉን ማራዘም እንደሆነ የቅንጀት አባላት ሊረዱት ይገባል ። የምዕራቡ አለምም ሆነ የኢትዮጵያ ሕዝብ የደርግን ኢሰባዊ ጭፍጨፋ በምንም አይነት አይረሱትም ዳግምም አይመኙትም። ለዚህም ነው ግልፅ በሆነ አቋም ቅንጀት እራሱን ከነዚህ የደርግ አራዊቶች ማፅዳት ያለበት። በሌላ በኩል ደግሞ በወያኔ ውስጥ ሲያገለግሉ የነበሩና ዛሬ በቅንጅት ውስጥ ያሉ ደግሞ ቅንጅትን እየከፋፈሉ መሆኑ ያደባባይ ሚስጥር ነው። አሁን ደግሞ የቅንጅት መሪዎች ከተፈቱ በኃላ ምን እንደሰሩ ሊጠየቁ ስለሆነ ቅራኔ በመፍጠር ሌላ አጀንዳ ለመፍጠር መራወጥ መጀመራቸው የሚታወቅ ነው።

ስሞኑን በፓልቶክ በደደቦች ሽንነ በቆራጥነት ደርግን የታገሉ ሁሉ ሲሰደቡ ነበር። የደርግ ካድሬዎች የሞቀ ኑሮችንን አደፈረሱብን በማለት እንደ እነ አያልነሽ ያሉ ታጋዮችን ሁሉ ሲሰድቡ ተሰምተዋል። አያልነሽ በቆራጥነት ደርግንም ወያኔንም ተዋግታለች። እሷን ከደርግ ጋር ያደረገችውን ትግል በአደባባይ መስደብ ምን ያህል ችግር በቅንጀት ውስጥ እንዳለ መገመት አያዳግትም። አያልነሽን ብቻ ሳይሆን ማንም ደርግን የተዋጋ ሁሉ እነዚህ በደርግ የተሳትፎ የድጋፍ ወረቀት እዚህ የደረሱ ካድሬዎች ጠላታቸው ደርግን የተቃወመ ሁሉ ነው። ያ ተንደላቀው የኖሩበት የደርግ ስርአት እንዲያከትም የታገለ ሁሉ ጣላታቸው ነው። ያ ህልማቸው ሳያስቡት በሊቀመንበራቸው ፍርጠጣ ቅዠት ሆኖ ቀርቶአልና ነው። እንዳነድቹ ዛሬ በሆላነድና ጀርመን የሚንደላቀቁ ካድሬዎች ምነው አየሽኝ ብለው ሽጉጥ መምዘዝ ጠባያቸው ነበር። አሁን ደግሞ ደርግን ተናገራችሁ ብለው መሳደብ ጠባያቸው ሆኑዋል። በሃገራችን ውስጥ ከአሁን ወዲያ የምንመሰርተው ስርአት እነዚህ የቀን አውሬዎች ሊያካትት አይገባም።

ሌላው ቧልት ደግሞ የሲቪሊቲ ክፍል ቀልድ ነው። ክፍሉ ውስጥ እንዳልገባ ለብዙ ግዜ ከተከለከልኩ በኃላ በወያኔ ምህረት ተደርጎልኝ ነው መሰል እንደገና እንደገባ ተፈቅዶልኛል። እንደተለመደው በዚህ ክፍል ስለሚሌኒየም ታላቅነት፣ ስለ አገሪቱ ኤኮኖሚ እድገት እንዲሁም ብዙ ብዙ ቀልዶች ከሰማሁ በኃላ ሁኔታውን ለመጠየቅ ወደ ኢትዮጵያ ብድውል አንድ ፈረሱላ በርበሬ 1000 ብር እንደገባ፣ ውሃ ለሃብታሞች እንደሚታደል፣ የኑሮ ውድነት ሰማይ እንደደረሰ፣ ነው ልሰማ የቻልኩት።በዚህ ወቅት ነው እነዚህ ቀልደኞች ኢኮኖሚው አደገ፣ ህዝቡ አለፈለት፣ ሊሉ የሚሞከሩት። በተለይም መብራትና ውሃ ዋጋ ጨምሮ ስንቱ ደሃ መክፈል ባልቻለበት ወቅት፣ ውሃ ላለው ብቻ በሚታደልበት ሁኔታ ነው ይህ ሁሉ ቧልት። ለዚህም ነው የዛሬውን ፅሁፌን ሚሊዬኒየሙን ባልጫ ልለው የተነሳሁት በርበሬውን እንደሆነ ለመግዛት የብዙው ሰው አቅም እንደማይችለው ነው።ዋጋ ለህዝቡ ያሰወደደው ከውጭ የሚሄደው በርበሬ አዘጋጁልኝ እያለ ለቤተሰቡ መደውል ከጀመረ ወዲህ ነው ተብሎ ነው የሚነገረው። ከውጭ ይዞት በሚገባው ገንዘብ እንደተጠየቀ የሚከፍለው ሆዳም የደሃውን ኑሮ ማበላሸቱ አይሰማውም። ለእርሱ የቆመ መንግስት ስላለው በርበሬ ይዞ መውጣት አይከለክለውም። ደሃው እንዳይበላ ይደረጋል እንጂ የወያኔን ጥሪውን ሰምቶ የመጣለትን ሆዳም ባዶ እጁን ልኮ አያሳፍረውም፣ ማስቀየም አይሞከርም። ይህ የሆነው ምድረ ሆዳም ለበአሉ ይገባል ስለተባለ የንግዱን አውታር የሚቆጣጠረው ወያኔ እንደ እህል ሰብል ብሎ ደርግ ባቋቋመው አይነት አዶስ መዋቅር አቋቁሞ የአዲስ አባባ ህዝብ ቅንጅትን በበምረጥ ላደረገው „ ጥፋት „ ሊቀጣው በወሰደው እርምጃ ነው።

ሌላው ደግሞ በኤርትራ የተቋቋመውን ህብረትን (AFD) የተቃወመው የፓልቶክ ክፍል የቅንጀት መሪዎች ከተፈቱ በኃላ ለሁለት ተሰንጥቋል። አንድ ክፍል ከወያኔ ጋር የሚደረገው ትግል ይቀጥል የሚለው ክፍል ሲሆን አንደኛው ደግሞ መሪዎቹ ከተፈቱ ከወያኔ ጋር መለሳለስ ጀምሮአል። በሚለሳለስው ክፍል ውስጥ መሪዎቹን ሲሰድቡ የነበሩት ወያኔዎች ግብተው እንዲፈነጩ ተፈቅዶላቸዋል። አቋም ነውና መለያየቱ ጥሩ ነው። በመከባበር መለያየትና አለመሰዳደብ ደግሞ አዋቂነት ነው። የጎላ ጭቅጭቅ ስላላየሁባቸው እንዲ በሰከነ መለያየታቸው ሊያስመሰግናቸው ይጋባል። ውስጥ አዋቂም ስላልሆንክ የተደበቀውን አላውቅም ግን ለጊዜው ምስጢሩ እስከሚወጣ በዚሁ እንቆይ ።

እስከሚቀጥለው

ስለኛ የሚስቡ ሁሉ በሰላም ይክረሙ